**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የወጣት ክንፍ ድርጅት** (ኢሕአፓ ወክንድ)
Ethiopian People's Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)

ግንቦት 2002 ዓ.ም.

በኢሕአፓ ወክንድ ለቀድሞ የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች የቀረበ የአክብሮት ጥሪ

የትናንቱ ኢሕአወሊ ፤ ኢትሀድ፤ ኢላአማ፤ ኢሴትድ፤ ኢጭወአማ … ወጣቶች የዛሬው ጎልማሶች አዛውንቶች ባጠቃላይ ሀገር ወዳድ አርበኞች የዛሬ 38 ዓመት ህልም ቃጭል በነበረበት፤ አመጽን ማደራጀት ቀርቶ ማሰብ ራሱ ወንጀል ተብሎ በተፈረጀበት ፤ ግራ ቀኙ፣ ላይ ታቹ፣ ጨልሞ ይቻላል ተራ ቃል ሳይሆን አደገኛና ለቅጣትም የሚዳርግ ሆኖ በተገኘበት በዚያ አስከፊ ዘመን የነገና የተነገ ወዲያ ብሩህ ኮከብ ከወዲሁ በተስፋ በማየት በሕዝብ ላይ ተንሰራፍቶ የነበረውን አሳፋሪ ስርዓት ማቸነፍ ይቻላል ብላችሁ ጨለማውን ለማስወገድ ክብሪት የጫራችሁ እንዲሁም  ዛሬም ላለነው ወጣት ትውልድ ህዝባዊና ሀገራዊ ትግል በመሆን ብርሃንን የፈነጠቃችሁ የኢሕአፓ አባላት ሆይ፤

- እንደሚታወቀው የዛሬ 19 ዓመት በጠመንጃ ኃይል በሥልጣን የተሰየመው ጠባብ ቡድን ሥልጣኑን ለማጠናከር ሕዝብን በቋንቋ በዘርና በሃይማኖት ከፋፍሎ በሕዝባችን አንድነት እንዲሁም በአገራችን ህልውና ና ሉዓላዊነት ይቅር የማይባል ግፍና በደል ዛሬም ድረስ በመስራት ላይ የሚገኝ በመሆኑ፡-
- መሰረታዊ የሆኑ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተገድበው፤ የዜግነት መብቶች ተነጥቀው፤ ሕዝቡ ከባርነት ያልተለየ ኑሮ  እንድንገፋ መደረጉና  ይህንንም ባደደባይ የተቃወሙና  መብት እንዲከበር የጠየቁ ጀግኖች ወንድሞቻችንና  እህቶቻችን በአረመኔው ወያኔ ቡድን የተገደሉ፣ የታሰሩ፣ አካላዊ ጉዳት የደረሰባቸውና  ብሎም ደብዛቸው የጠፋ መሆኑንና ይህም ግፍ አሁንም እየቀጠለ በመሆኑ፣
- ሀገራዊ ኃላፊነት በብቃት ልንወጣ የምንችለውን ወጣቶች በትምህርት ቤት ተቋማት በሌሎች ቦታዎች  በዘርና በሃይማኖት አለፍላጎታችን እንድንከፋፈል መደረጉ፣

የአንድነታችን ሰንሰለት የሆነውን ኢትዮጵያዊነት ለማላላትና ለመበጣጠስ የሚደረገውን አይን ያወጣ ግፍ የሚሸከም ጫንቃ ከእንግዲህ የማይኖረን በመሆኑ  እነሆ ግፍ ይብቃን ብለን እኛም እንድ አባቶቻችንና እንደ እናቶቻችን ለሀገራችን ኢትዮጵያ የክብር ሞት ለመሞት ቆርጠናል፣ ተዘጋጅተናል።

የቀድሞ የኢሕአፓ አባላቱና ደጋፊዎቹ ሆይ

ያ ኢትዮጵያን በዴሞክራሲያዊ ጎዳና ቀጥታ እንድትኖር ለማድረግ ዘመናትን ያስቆጠረው ትግላችሁ ለምድሪቷና ለሕዝቧ ነጻነትና እኩልነት በደማችሁ የገበራችሁ፤ አጥንታችሁን የከሰከሳችሁ፤ የታሰራችሁ፤ እንግልት የደረሰባችሁ፤ የተሰደዳችሁ ለዚህ ሁሉ ፈታኝ ህይወት አብሪ ጥይት የሆናችሁ፤ ዛሬ ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች ከትግሉ ርቃችሁ የምትገኙ በሙሉ እኛ ወጣት ልጆቻችሁ በክብር የከፈላችሁትን መሰዋእትነት በአዲስ ጉልበትና ኃይል አጠናክረን በመነሳት በወያኔም ሆነ በባዕዳን የተቀደደውን ያገራችንንና የሕዝባችንን የክብር ሰንደቅ ለመስፋት በምናደርገው ሕዝባዊ የአይቀሬነት ፍልሚያ ለትግላችን ደጀን በመሆን ከጎናችን እንድትቆሙልን በማለት ኢወክንድ ጥሪውን ያስተላልፋል።

እኛ ወጣቶች በክብር የተሰጠንን ሀገራዊ ኃላፊነት በደማችን እናስከብራለን!!

ሕዝባችን መብቱን በትግሉ ይቀዳጃል!!

እናቸንፋለን!!

Tel 202-291-5832  P.O.Box 56068  Washington DC 20040  e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com